የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No.62
ADDIS ABABA 2nd August, 2004

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፰/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተከሰተውን ግጭት ለሚያጣራ ኮሚሽን የተፈቀደ የበጀት አዋጅ.... ገጽ... ፪ሺ፰፻፵

CONTENTS

Proclamation No. 418/2004

A Proclamation to ratify the budget for the inquiry commission to investigate the incident occurred in Gambella Regional State on December 13 Ratification Proclamation. ... Page 2840

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፰/፲፱፻፺፮

### ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተከሰተውን ግጭት ለሚያጣራ ኮሚሽን የተፈቀደ የበጀት አዋጅ

ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተከሰተውን ግጭት የሚያጣራ ገለልተኛ የሆነ አጣሪ ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር ፫፻፺፰/፲፱፻፺፮ የተቋቋመ በመሆኑ፤

ኮሚሽኑ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል፣ በጀትና ጽህፈት ቤት ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚሟሉለት በአዋጅ ቁጥር ፫፻፺፰/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፮ ሥር የተደነገገ በመሆኑ፤

ኮሚሽኑም የተጣለበት ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይችል ዘንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበጀት ጥያቄውን መመለስ እንዳለበት በመታመኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ፵፩ኛ መደበኛ ስብሰባ የበጀቱን ጥያቄ ተቀብሎ ያፀደቀው በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO. 418/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE BUDGET FOR AN INQUIRY COMMISSION TO INVES- TIGATE THE INCIDENCE OCCURRED IN GAMBELLA REGIONAL STATE ON DECEMBER 13, 2003

**WHEREAS,** an independent inquiry commission to investigate the incident occurred in Gambella Regional States on December 13, 2003 was established by proclamation No.398/2004;

**WHEREAS,** the House of People's Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has assumed the responsibility of fulfilling the necessary staff, office and budget of the commission under Article 6 of the proclamation;

**WHEREAS,** the commission to discharge the responsibility visited upon it the House of People Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has to reply the Budgetary Question of the commission;

**WHEREAS,** the House of People Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia at its 41 regular session held on 6th July 2004 has accepted and ratified the budget;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2:30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተከሰተውን ግጭት ለሚያጣራ ኮሚሽን የተፈቀደ የበጀት አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፰/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. በጀቱ ስለመጽደቁ

፩/ ኮሚሽኑ ሥራውን ተገቢ በሆነ መንገድ ይሠራ ዘንድ በአጠቃላይ ብር ፬፻፶፫ሺ.፪፻፴፱ (አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሳ ዘጠኝ ብር) በጀት ተፈቅዶለታል።

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተፈቀደለትን በጀት የሚጠቀመው ከዚህ አዋጅ ጋር አባሪ ተደረጎ በተያያዘው መሠረት ይሆናል፣

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሃላፊነት

፩/ በአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው በጀት ሚኒስቴሩ ከመንግሥት የመጠባበቂያ በጀት ለኮሚሽኑ ይከፍላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወጪ አድርጎ የከፈለውን ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋል አለመዋሉን ለማረጋገጥ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (10) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is here by proclaimed as follows.

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "the Proclamation to ratify the budget for the inquiry commission to investigate the incident occurred in Gambella Regional State on December 3, 2003."

## 2. Approval of the Budget

1/ The commission to implement the task vested on it the total amount of Birr 453,239.00 (four hundred fifty three thousand two hundred thirty nine Bir) has been allowed.

2/ The commission shall utilize the budget in accordance with the schedule attached there to.

## 3. The Responsibility of Ministry of Finance and Economic Development

1/ The budget indicated under Article 2 (1) of this proclamation shall be paid by the ministry out of the budget reserved for unforeseen expenditure;

2/ The ministry of finance and economic development is empowered to monitor whether the money dispersed in accordance with the objective set forth.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the Federal Negarit gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of August, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**